**ያቁሙ**

# የንክኪ ቅድሚ ጥንቃቄዎች

**ጎብኚዎች** ከመግባታቸው በፊት ከነርስ ጋር ይገናኛሉ።

## ከመግባትዎ በፊት፡



**እጅዎን ይታጠቡ**



**ጋዎንና ጓንት ያድርጉ**

## ሌላ መስፈርቶች፡



**ለሕመምተኛ ብቻ የተፈቀዱ ወይም ሊጣሉ የሚችሉ መገልገያዎችን ይጠቀሙ።**

**የጋራ መገልገያዎችን በፀረ ተባይ ያጽዱ።**

***ቅድሙ ጥንቃቄ ከተቋረጠና ክፍሉ ከጸዳ በኋላ ምልክቱ Environmental Services (በአካባቢ አገልግሎት) ሠራተኞች እንዲነሳ ይደረጋል።***

Washington State Hospital Association

Washington State Department of HEALTH

7/30/2024

**ከበር ውጪ ያሳዩ። ታካሚው ከወጣ፣ ክፍሉ ሙሉ በሙሉ ከጸዳ በኋላ ምልክቱን ያንሱ።**

# የንክኪ ቅድሜ ጥንቃቄዎች

## የግል መከላከያ መሣሪያዎች (PPE)

***በመደበኛ ቅድመ ጥንቃቄዎች መሠረት ለሎች የግል መከላከያ መሣሪያውች በተጨማሪ፣ በመጀመሪያ ገጽ ላይ የተዘረዘሩትን የግል መከላከያ መሣሪያዎች በመያዝ፣ የሚከተሉት ቅደም ተከተሎች ለሁሉም የግል መከላከያ መሣሪያዎች ማሳያዎች ናቸው።***

| የግል መከላከያ መሣሪያዎች (ልገሳ) ማድረግ። | የግል መከላከያ መሣሪያዎች ማውለቅ |
|---|---|
| **1.** የእጅ ንፅህናን ያከናውኑ<br>**2.** መከላከያ ጋዋን፣ አስተማማኝ የሆነ ጥምጣም/ከረባት ያድርጉ<br>**3.** መተንፈሻ ወይም የፊት ጭምብል ማድረግ፣ ተስማሚና በትክክል መግጠማቸውን ማረጋገጥ።<br>**4.** የፊት መሸፈኛ ወይም መነጽር ይጠቀሙ<br>**5.** ጓንቶችን ያድርጉ | **1.** ከታካሚ ክፍል ውስጥ ከሆናችሁ፣ እጅን በማይበክል መልኩ ጓንቶችን ያውልቁ።<br>**2.** ጋዎን ያውልቁ - ከረባት/ጥምጣም ይፍቱ፣ ሊጣሉ ለሚችሉ ጋዎኖች ማሰሪያ የሚውል ከሆነ ከረባቱን ይቁረጡ። እያንዳንዱን ክንድ ለማስወገድ አንድ ትከሻን በአንድ ጊዜ በመያዝ ያስወግዱ። ካወለቃችሁ በኃላ በመጠቅለል ትክክለኛ ማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጡ። አሁን ከክፍሉ መውጣት ትችላላችሁ።<br>**3.** እንደወጣችሁ፣ የእጅዎን ንጽሕና (የሚታይ ቆሻሻ፣ የሰገራ ንክኪ ወይም ከቅድመ-ጥንቃቄ መጓደል ንክኪ አጋጥምዎት ከሆነ፣ ሳሙና ውኃ ይጥቀሙ) ያከናውኑ።<br>**4.** የፊት መሸፈኛ/መነጽር ያውልቁ - ተበክሎ ሊሆን ስለሚችል የዓይን መከላከያ መጀመሪያ ክፍል አይንኩ።<br>**5.** መተንፈሻ/የፊት ጭምብል በትክክል በመያዝ ያውልቁ - ተበክሎ ሊሆን ስለምችል የፊት ለፊት ክፍል ከመንካት በመቆጠብ እንዳይበክል አድርገው ተገቢ በሆነ መልኩ ይጣሉ።<br>**6.** የእጅዎን ንፅህና ደጋግመውይጠብቁ። |

**እንደ የሚከተሉት ሁኔታዎች ለመጠቀም፡- (የተቋሙን ፖሊሲ ይመልከቱ)**

- እንደ ተቋሙ ፖሊሲ ከሆነ ብዙ-መድኃኒት ተቋቋሚ ኦርጋኒዝሞች (MDRO)ና የኢፒደሚኦሎጂካል ፓቶጀንስ ጉዳይ
- እከክ/ቅማል
- ያለማቋረጥ ፈሳሽ የሚያፈስ ቁስል/የመግል ቁስል

**የታካሚ ምደባ**

- ታካሚን የግል ክፍል ወስጥ ይመድቡ። የማይገኝ ከሆነ፣ ለጋራ መገልገያ መመሪያዎችን ይከተሉ።

**ምግቦችና ዕቃዎች**

- ልዩ ቅድመ ጥንቃቄዎች የሉም። የማዕድ ቤት ዕቃዎች ዕቃ ማጠቢያ ውስጥ ይጠቡ።

**የቆሻሻ እና የአልጋ ልብስ ንጽሕና አጠባበቅ**

- አልጋ ልብስ ከታካሚ ክፍል ውስጥ ያስቀምጡ። ከመጠን በላይ ንክኪና አልጋ ልብስ ማራገፍን ያስወግዱ። ለባዮአዛርድ ቆሻሻ፣ ምድብ ቢ የህክምና ቆሻሻ መመሪያዎችን ይከተሉ።

**ክፍልን ማጽዳት**

- ተገቢ ከሆነ የአየር ዝውውር በኃላ በሆስፒታሉ አሠራር መሠረት የግል መጋረጃ ቅየራ ጨምሮ መደበኛ የጽዳት ሂደቶች ይካሄዳሉ።

**መሣሪያና አቅርቦቶች**

- ክፍል ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያና አቅርቦቶችን ብቻ ይቀመጡ።
- ለታካሚ ብቻ የተፈቀዱ ወይም ልጣሉ የሚችሉ መገልገያዎችን ይጠቀሙ።
- በተቋሙ ፖሊሲ መሠረት ድጋሚ የሚያገለግሉ መሣሪያ/የታካሚ ክፍል ፀር-ተባይ መርጨትና ማጽዳት።

**ትራንስፖርት**

- የታካሚውን የመውጫ ቅድመ ጥንቃቄ ሁኔታ ለተቀባይ ክፍል ማሳወቅ።
- ታካሚው እጁን መታጠብ አለበት። ታካሚው ጋዎን ወይም ንጹህ አንሶላ እንዲለብስ ማድረግ እና በበሽታ የተጎዱ ቦታዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ማሸግ(ለምሳሌ ክፍት/ፈሳሽ ያለው ቁስል)
- አጓጓዡ ከታካሚው ክፍል ከመውጣቱ በፊት እጁን መታጠብና የግል መከላከያ መሣሪያ ያወጣል። በመጓጓዣ ጊዜ ቀጥተኛ ግንኙነት የሚጠበቅ ከሆነ ተገቢውን PPE ይልበሱ።
- የትራንስፖርት መኪናን ፀረ-ተባይ በመርጨት ያጽዱ።

***በተቋሙ ፖሊሲ መሠረት ቅድሙ ጥንቃቄ ያቋርጡ፡***
***ቅድሙ ጥንቃቄ ከተቋረጠና ክፍሉ ከጸዳ በኋላ ምልክቱ Environmental Services (በአከባቢ አገልግሎት) ሠራተኞች እንዲነሳ ይደረጋል።***

**420-587 April 2024 Amharic**

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለማግኘት፣ ወደ 1-800-525-0127 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸግራቸው ደንበኞች ወደ 711 (Washington Relay) መደወል ወይም ወደ doh.information@doh.wa.gov ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

Washington State Hospital Association

Washington State Department of HEALTH

7/30/2024